# ግብፅ የቅኝ ግዛት ውሎችን መናፈቋ ያዋጣት ይሆን?

ሸረፋ ከድር

ksherefa@yahoo.com

01/26/14

በህዝብ የተመረጡትን የቀድሞው የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት መሐመድ ሙርሲን በወታደራዊ ኃይል ከስልጣን አስወግዶ በትረ-ስልጣኑን የጨበጠውና በጄኔራል ሲሲ ግርዶሻዊ አመራር የሚዘወረው 'አዲሱ' የግብፅ መንግስት ከመሰንበቻው አስደማሚ አጀንዳ ይዞ ብቅ ብሏል። አዎ! ዓባይ ወንዝን ፍትሐዊ በሆነና በሰለጠነው የ21ኛው ክፍለ-ዘመን አስተሳሰብ በጋራ ለመጠቀም ለሶስት ዙሮች ያህል ከሱዳንና ከኢትዮጵያ ጋር ሲደራደር፣ መሐል ላይም ሳንካ ሲፈጥር የነበረው የካይሮ አስተዳደር፤ የቀደምት የሀገሪቱን ገዥ መደቦች አሮጌ ካባ ተከናንቦ "የታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጉዳይ ወደ ተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለመውሰድ ተዘጋጅቻለሁ" የሚል አባባልን 'እንካችሁ' ማለቱ ብዙዎችን ግርምት ውስጥ ከትቷል።

በሀገሪቱ የውሃና የመስኖ ልማት ሚኒስትር ቃል አቀባይ ካህሊድ ዋሲፍ የተነገረውና "ግብፅ የህዳሴው ግድብ ግንባታን ፈፅሞ አትፈቅድም፡፡ ይህንን ለማሳካትም ኢትዮጵያ ለግድቡ ምንም ዓይነት የውጭ ዕርዳታ እንዳታገኝ ግፊት እናደርጋለን" መባሉ፤ እርግጥም ግብፅ እስካሁን ድረስ ለምን ከሱዳንና ከኢትዮጵያ ጋር ስትደራደር እንደቆየች ግልፅ ይመስለኛል፡፡ ይኸውም 'እስካሁን ድረስ ስንደራደር ብንቆይም የኢትዮጵያ መንግስት ሊሰማን ስላልቻለ ጉዳዩን ወደ ዓለም አቀፉ መድረክ አምጥተነዋል' በማለት ርካሽ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት ነው። ግና ይህ አካሄድ የሚያስኬድ አይደለም። ምክንያቱም የግብፅ ሃሳብ ዕውነታ ቢኖረው ኖሮ ቢያንስ በድርድሩ ወቅት የጉዳዩ ባለቤት የነበረችውን ሱዳንን እንኳን የሚያሳምን ስላልነበረ ነው። እናም በቀደምት የሀገሪቱ መሪዎች ፅላሎታዊ የቅኝ አገዛዝ መንፈስ እየተመራ ጉዳዩን ለመንግስታቱ ድርጅት አቀርባለሁ ማለቱ የሚያስገርም ነው።

ያም ሆነ ይህ ግን እዚህ ላይ ‘ግብፅ የቅኝ ግዛት ውሎችን መናፈቋ ያዋጣት ይሆን?’ የሚል ጥያቄን ማንሳት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ለምን ቢሉ ትናንትም የግብፅ ገዥ መደቦች ውሎቹን በሀገራችን ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ገቢራዊ ለማድረግ ያልማሱት ጉድጓድ ስላልነበረ ነው–ምንም እንኳን ይህ ጥረታቸው መና ሆኖ የቀረ ቢሆንም። ታዲያ ላነሳሁት ጥያቄ ምላሽ ከመስጠቴ በፊት በቅድሚያ ግብፆች እንደ ትናንቱ ዛሬም በመንግስታቸው በኩል ያነሱትን ነጥቦች በቅድሚያ መመልከቱ አግባብነት አለው። ቃል አቀባዩ ካህሊድ ዋሲፍ፤ ግብፅ በዓባይ ወንዝ ላይ በዓለም አቀፍ ሕግ የተከበረና የተረጋገጠ መብት እንዳላት፣ ማናቸውም የተፋሰሱ አገሮች ተፋሰሱን በመጠቀም ወደ ልማት መግባት ሲፈልጉ በቅድሚያ ግብፅን የማማከርና ይሁንታ የማግኘት ግዴታ እንዳለባቸው፣ ይሁንና ኢትዮጵያ ይህንን ግዴታ በመጣስ የህዳሴውን ግድብ ግንባታ መጀመሯ በራሱ ሕግን የጣሰ ተግባር በመሆኑ ሀገራቸው ከድርድሩ ራሷን ማግለሏን ተናግረዋል። ግና እነዚህ አባባሎች ሲጨመቁ አንድ ጠብታ ሃቅ ይወጣቸው ይሆን?–እስቲ አብረን እንያቸው።…

የግብፅ መንግስት ‘በዓባይ ወንዝ ላይ በዓለም አቀፍ ህግ የተረጋገጠልኝ ህግ አለ’ ሲል፤ እ.ኤ.አ. የ1929 እና የ1959 ዓ.ም ውሎች ሊከበሩልኝ ይገባል ማለቱ ግልፅ ነው። እነዚህ ውሎች ግን በሰለጠነው ዘመን እሳቤ የማይሰሩ ብቻ ሳይሆኑ ሀገራችን ስምምነቶቹን ያልፈረመችና ዕውቅና የማትሰጣቸው በመሆናቸው በማናቸውም ዓለም አቀፍ መስፈርቶች ተቀባይነት የላቸውም።

እንደሚታወቀው የአባይ ውኃን የመጠቀም መብት ቅኝ ገዥዎቹ ባዘጋጁትና በቀይ ካርድነት ሲያገለግል በቆየው እ.ኤ.አ የ1929 እና 1959 “የናይል ውኃ አጠቃቀም ስምምነት” ተገድቦ ቆይቷል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም “የውሾን ነገር ያነሳ…” እንዲሉ የተፋሰሱ ሀገራት በመብታቸው እንኳንስ ሊጠቀሙ ቀርቶ ሃሳብ እንዳላቸው እንኳን ቢሰማ ሊደርስባቸው የሚችለውን ችግር ቀድመው የሚያውቁት ስለሆነ “አይነኬ” ሆኖ ዘመናትን ተሻግሯል፡፡ ምንም እንኳን ግብጾች የውሃው “የታሪካዊ መብት” ተጠቃሚዎች እንደሆኑና ሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት ወንዙን እንዳይጠቀሙ መብታቸውን ገድበው በመኖራቸው ሳቢያ ዓባይን እንደ ግል ሀብታቸው ቢቆጥሩትም፤ በእኩልነት፣ በፍትሐዊነትና በምክንያታዊነት ውኃውን የመጠቀም መብት ከላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት በኩል መነሳቱ ግድ ሆኗል–ሁሉም ነገር ባለበት አይቆምምና።

ሀገራችን የናይል ወንዝ አጠቃቀምን አስመልክቶ በእንግሊዝና በግብጽ የተካሄደው የ1929ኙ ስምምነትንም ይሁን በግብጽና በሱዳን መካከል የተፈረመው የ1959ኙን ስምምነት አታውቀውም። አለማወቅ ብቻ ሳይሆንም ተቀባይነት እንደሌለውም ስታሳውቅና አቋሟን ስታንጸባርቅ መቆየቷ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስምምነቱን ኢ-ፍትሃዊነትንም እንዲሁ፡፡ ይህ ሀገራዊ አስተሳሰብ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ መንግስታት ሁሉ በአባይ ውኃ አጠቃቀም ዙሪያ ተመሳሳይ አቋም ሲያንጸባርቁ ቆይተዋል፡፡ እርግጥም "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" እንደማይታሰብ ሁሉ፣ ሁሉንም የተፋሰሱን ሀገራት ያላከተተውና በሁለቱ የታችኛው ተፋሰሱ ሀገራት መካከል የተካሄደው ስምምነት ተቀባይነት የሌለው መሆኑ እርግጥ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን ይህ የላይኛው ተፋፈስ ሀገራት አቋም ሰሚ ጆሮ ማግኘት አልቻለም፡፡ በተለይም በግብጾች በኩል ይህ "የቅኝ ገዥዎች" ስምምነት የማይጣስ መሆኑን ከመግለፅ ባለፈ፣ ከዛቻ አዘል ማስፈራሪያዎች ጋር ሲሰነዘር ቆይቶ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ይህ ጉዳይ ኢትዮጵያን ዋነኛዋ የትኩረት አቅጣጫ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ዓለም ያወቀው ሃቅ ነው፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ግብጾች ሊያውቁት የሚገባው ነገር ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን አሳልፋ የምትሰጥበት ጊዜ ያከተመ መሆኑን እንዲሁም በእኩልነትና ምክንያታዊነት በጋራ የመጠቀም መርህ ጽኑ አቋሟ ሊቀለበስ እንደማይችል ነው፡፡ ለነገሩ "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም" እንደሚባለው እነዚህ በሙባረክ ዘመን እሳቤ የሚዳክሩ አሮጌ ፍራሽ አዳሽ ግብፃውያን የኢትዮጵያ አቋም በሚገባ ስለሚያውቁት እዚህ ላይ ብዙ ማለት አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡

ይሁንና እንደኔ... እንደኔ በአሁኑ ወቅት ቅኝ ገዥዎቹ በዚያን ዘመን ለፈጸሙት በደል ይቅርታ በመጠየቅና ለተበዳዮች ካሳ እየከፈሉ እንደሚገኙ ሁሉ፣ ግብጾችም የቅኝ ገዥዎቹን የታሪካዊ ባለመብትነት ሰነድ ለመከራከሪያነት ማቅረቡን (ለዚያውም ወደ መንግስታቱ ድርጅት ለመውሰድ ዝግጅት አጠነቅቀናል ማለታቸውን) ትተው ለዘመናት "የበይ ተመልካች" ላረጓቸው የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት ይቅርታ መጠየቅ በተገባቸው ነበር። ከዚህ ባለፈ ግን በስልጡኑ 21ኛው ክፍለ ዘመን እየኖሩ የ19ኛው ክፍለ ዘመንን አሮጌና ተቀባይነት የሌላቸው ህጎችን እያጣቀሱ ለመከራከሪያነት ማቅረብ በየትኛውም መስፈርት ቅቡል አለመሆናቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ለምን ቢባል፣ ግብፅ ዛሬም በቅኝ ገዥዎች ህግ እተዳደራለሁ የምትል ከሆነ፣ አሁንም እንግሊዝ ትግዛኝ የማለት ያህል በመሆኑ ነው።

ይህ ደግሞ በስልጣኔ ድባባ በተጥለቀለቀችው ዘመናዊ ዓለማችን ውስጥ የሚታሰብ አይደለም–በእሳቤዎቹ መካከል ቢያንስ የሁለት መቶ ዓመት ልዩነት አለና።

ውድ አንባቢዎቼ! ሀገራችን ለመስኖና ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫነት ያሚያገለግሉ በርካታ ወንዞች ያላት በመሆኗ ሳቢያ የምስራቅ አፍሪካ “የውሃ ማማ” /water Tower/ በሚል ስያሜ ብትታወቅም፤ በተፈጥሯዊ የውሃ ሀብቷ የመጠቀም መብቷ ተገድቦ መቆየቱ ከማናችንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህ ደግሞ በምክንያትነት የሚጠቀሱት ሀገሪቱን ጨምድዶ ይዞ የነበረው የከፋ ድህነት እንዲሁም ያለፉት መንግስታት የአስተሳሰብ ውስንነት መሆናቸው እሙን ነው፡፡ ታዲያ ይህ ሁኔታ ዛሬ ላይ የለም።

በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያ እውን የማድረግ ራዕይን የሰነቀው የኢፌዴሪ መንግስት፤ የህዝቡን ልማታዊ ተጠቃሚነትን በየደረጃው የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ቀርፆ ለውጤት በመብቃቱ ከላይ የተጠቀሱን ሁለት ተግዳሮቶች በአስተማማኝ ሁኔታ መፍታት ችሏል። በዚህም የዘመናት ቁጭታችን የሆነውን በተፈጥራዊው የውኃ ሀብታችን የመጠቀም መብታችንን በበቂ ዲፕሎማሲያዊ ክህሎት ታጅቦ በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡

እርግጥ የግብጽ መንግስታት በናይል ውኃ የብቻ ተጠቃሚነትን እንደ ታሪካዊ መብት ባለቤትነት ሲያጣቅሱ መደመጣቸው የሚገርም ጉዳይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የተፋሰሱ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት መብትን በተለያዩ ዘዴዎች እያደናቀፉ ዘመናትን ሲቆጥሩ የኖሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ለማንኛውም ትናንት ዛሬ አይደለምና ሀገራችን ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት እያስመዘገበች በመሆኑ፤ በተፈጥሯዊ የውሃ ሀብቷ በመጠቀም መብቷ በማትደራደርበት ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ እናም ነህገሯ ለምታከናውናቸው የልማት ስራዎች የማንንም ይሁንታ እንደማትፈልግ ካይሮዎች ሊያውቁት ይገባል። የትኛውም ዓለም አቀፍ ህግ በፍትሐዊ መንገድ የሚከናወኑ ልማትና ዕድገትን አይፃረርምና። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት እየተጠናከረ የመጣው የህዝቧ የልማት ቁርጠኝነት እንዲሁም መንግስት የሚያከናውናቸው ሁለንተናዊ የልማት ስራዎች ዘላቂና ከባቢያዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ መሆን ችለዋል፡፡ ይህ ተግባሯም ከጋራ ተጠቃሚነት መርህ ውጭ አሮጌና ዘመን ያለፈባቸው አስተሳሰቦች ዋጋ ቢስ መሆናቸውን ያረጋገጠ ነው፡፡

ለዚህም ነው ኢትዮጵያ አሮጌው የቅኝ ገዥዎች ስምምነት የተፋሰሱ ሀገራትን በውሃው እኩል ተጠቃሚነት እንዲሆኑ በሚያደርገው የኢንቴቤው የትብብር ስምምነት ማዕቀፍ መተካት ለአማራጭና ለድርድር የማይቀርብ መሆኑን በየጊዜው በመግለፅ ላይ የምትገኘው፡፡ ታዲያ ሀገራችን ስምምነቱን ስትቀበል በምክንያታዊነት ላይ ተመስርታ መሆኑን ልብ ማለት ያሻል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ የኢንቴቤው የትብብር ስምምነት የሁሉንም የተፋሰሱን ሀገራት መብት የሚያስጠበቅና እኩል ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ እንጂ ልክ እንደ ቅኝ ገዥዎቹ ስምምነት በጣት ለሚቆጠሩ ሀገሮች መብት የቆመ አለመሆኑን ስለምትገነዘብ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ስምምነቱ በዓለም አቀፉ የውሃ አጠቃቀም መሰረታዊ መርሆዎች ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀና ህጋዊ መሰረት ያለውና ህገ ወጥ ስምምነቶችን በተለይም የቅኝ ግዛት ውሎችን በጽኑ የምትቃወም ሀገር ስለሆነች ነው። እናም አሮጌው ስምምነት በአዲሱ የመተካቱ አስፈላጊነት ከፍተኛ እንደሆነ ታምናለች፡፡ በመሆኑም ዕውቅና የምትሰጠው አብዛኛው የተፋሰሱ ሀገራት ለተስማሙበት የኢንቴቤው ስምምነትን እንጂ እንደ መከራከሪያ ነጥብ በግብፆች ለሚጠቀሰው የቅኝ ገዥዎች ሰነድ አይደለም፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን የትኛውም ወገን ያሻውን ቢልም፤ ሀገራችን እንደ ማንኛውም ሀገር በውሃ ሃብቷ በመጠቀም ህዝቦቿን ከድህነት የማላቀቅ መብት እንዳላት ማወቅ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው ኢትዮጵያን ጨምሮ ሁሉም የላይኛው የናይል ተፋሰስ ሀገራት ህዝቦቻቸውን ከድህነት የማውጣት የቤት ስራ ፊታቸው ላይ ተደቅኖ ይገኛል፡፡ ይህን የቤት ስራቸውን በብቃት ለመወጣት ደግሞ ሁሉንም የተፈጥሮ ሃብታቸውን በተገቢው ሁኔታ አልምተው መጠቀም ይኖርባቸዋል። እናም ከተፈጥሮ ሃብታቸው አንዱ የሆነውን ውሃ ለልማት የማዋል ጉዳይ ጊዜ የሚሰጡት አይደለም–ነገሩ የሞት ሽረት ጉዳይ ነውና።

ሀገራቱ በውሃ ሀብታቸውን ተጠቅመው የምግብ ዋስትናቸውን እንዲሁም የሃይል አቅርቦትን በማሳደግ ለኢንዱስትሪው ኢኮኖሚ ምቹ ሁኔታ መፍጠርን ዋነኛውና ወሳኙ አማራጭ አድርጓል፡፡ በዚህም የዘመናት በደላቸውን ወደ ጎን በመተው በሆደ ሰፊነት በውሃው እኩል ተጠቃሚነት ላይ ለሁለት አስርት ዓመታት ሲደራደሩ መቆየታቸው የሚታወስ ነው፡፡ ታዲያ ይህ ሂደት አንድ ትልቅ ግንዛቤን ያስጨበጠናል፡፡ እርሱም የተፋሰሱ ሀገራት

በውሃው የጋራ ተጠቃሚነት ላይ ብቻ መመስረታቸውን እንዲሁም ይህ ሃሳባቸው ማንንም ለመጉዳት የታሰበ አለመሆኑን ነው፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው አንዱን ተጠቃሚ ሌላውን ተጎጂ ያደረጉት ሁለቱም የቅኝ ገዥዎች ስምምነቶች በዋነኛነት ከግብጽ በስተቀር ሌሎቹን የተፋሰሱ ሀገራት ያገለሉና በሃይል ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ከብቀላ ነጻ የሆነውና የተፋሰሱ ሀገራት በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሰረተው የኢንቴቤው የስምምነት ማዕቀፍ፤ የውሃ ባለሀብቶቹን የላይኛው ተፋሰስ ሀገራትንም ይሁን ዋነኛ ተጠቃሚ የነበረችውን ግብፅን ያጠቃለለ ሰጥቶ መቀበል አካሄድን የተከተለ መሆኑ ከላይ ለገለፅኩት እውነታ ሁነኛ አስረጅ ነው፡፡

እንደሚታወቀው በዋነኛነት ግብጽንን ብቸኛ ተጠቃሚ ሲያደርግ የቆየው የ1929ኙና 1959ኙ ስምምነት፤ በግንባር ቀደምነት ከካይሮ በስተቀር ሌሎቹን የተፋሰሱ ሀገራት "አንድም ጠብታ ውሃ" መጠቀምን የሚከለክልና ለዘመናት የተሸጋገረ የግልኝነት አስተሳሰብን የሚያራምድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የግብጽ መንግስታት ባረጀው አስተሳሰብ መመራት አለብን የሚለው ግትር አቋማቸው ዛሬም ቀጥሏል፡፡ ዳሩ ግን አስተሳሰቡ ጊዜንና ወቅትን ያላገናዘበ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሆኖ ልክ እንደ በረዶ ዘመን ሰው የማሰብ ያህል ነው፡፡ በእኔ እምነት የዚህ እሳቤ ምንጭ የላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት በውሃ ሀብታቸው የመጠቀም አቅም እንዳይኖራቸው በግብፅ አማካኝነት በተሸረበው ሴራ ለድህነት ተጋልጠው የቆዩ በመሆናቸው፤ ዛሬም በራሳቸው አቅም የመስራቱ ጉዳይ የማይታሰብ እንደሆነ ተደርጎ ስለሚታይ ነው፡፡ ለዚህም ነው ግብፆች የሚሉትን ሲያጡ የህዳሴው ግድብ የፋይናንስ እጥረት ተጋርጦበታል የሚል የበሬ ወለደ ድርሰት እያስደመጡን ያሉት።

ያም ሆነ ይህ ግን የተፋሰሱ ሀገራት ከድህነትና ኋላቀርነት ለመላቀቅ በሚያደርጉት ርብርብ የውሃ ሀብታቸውን የመጠቀም መብት አስፈላጊነት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ በርካታ ዓመታትን በምክክርና በድርድር አሳልፈዋል። በዚህም የላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት መብትን ለሚጻረረው "እኛ ስንጠቀምብት ኖረናል አሁንም እንጠቀምበት" ለሚለው የቅኝ ግዛት ውል ዓይን ያወጣና ድፍረት የተሞላበት የግለኝነት ምልከታ ወደ መቃብሩ ለመሸኘት የሚያስችለውን የናይል የትብብር ስምምነት ማዕቀፍን ይፋ አድርገዋል። በመሆኑም የሌላውን የውሃ ዋስትና የማይጻረር እንዲሁም በፍትሃዊነትና በምክንያታዊነት መርህ የመጠቀም መብታቸውን በማረጋገጥ ያለባቸውን የኤሌትሪክ ሃይል

እጥረት ለመቅረፍ ስምምነት ላይ መድረስ ችለዋል– ምንም እንኳን በግብፅ በኩል ይህ ሰናይ እሳቤ ተቀባይነት ሳያገኝ ዛሬም ድረስ ቢቆይም፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። እርሱም "ዕውንየግብፅ የውሃና የመስኖ ልማት ቃል አቀባይ እንደሚሉት ግድቡ ሀገራዊ ጥቅማቸውን ይጎዳልን?" የሚል ነው። እሰቲ ለማንኛውም ሃቁን በመጠኑ እንመርምረው– ከአሉባልታ ይልቅ ሃቅ ጉልቶ መውጣቱ አይቀርምና። እንደሚታወቀው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እንዲከናወን የተወሰነው ከጎረቤት ሀገር ሱዳን ድንበር 20 ኪሎ ሜትር ተጠግቶ ነው፡፡ ይህም ግድቡ ለመስኖ አገልግሎት ሊውል እንደማይችል ያሳያል።

እናም ውሳኔው የኤሌትሪክ ሃይልን የማመንጨትና የሃይል አቅርቦትን በማሳደግ ሀገራዊ ልማትን ከማፋጠን ውጪ፣ እነርሱ እንደሚሉት "ለመጉዳት" ያለመ እንዳልሆነ በቀላሉ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ ሌላ ምክንያት ላክል፡፡…የኤሌትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድቦች ሃይልን ከማመንጨት ባሻገር፣ አንድ ጠብታ ውሃም ቢሆን እንደማያባክን ሁሉም ጠንቅቆ የሚያውቀው ዕውነታ ነው፡፡ ለዚህም ከሀገራቱ የተውጣጡ የሙያተኞች ቡድን በግድቡ ዙሪያ ጥናት ሲያካሂድ ከቆየ በኋላ ባቀረበው ሪፖርት፣ ግድቡ የማንኛውም ሀገር ጥቅምን የማይነካና የጉዳት መጠኑም እጅግ በጣም አነስተኛ መሆኑን አስረድቷል፡፡ ይልቁንም ግድቡ በታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት ውስጥ በየዓመቱ ሲደርስ የቆየውን ከፍተኛ የውሃ ትነት መጠን የሚያስቀር በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ አስምሮበታል። እናም ይህ ምስክርነት የግብፅን "የይጎዳኛል" እሳቤ ፉርሽ የሚያደርገው ነው።

ዳሩ ግን ግብፆች የሌለን ነገር ለምን እንደሚያጦዙ ግልፅ ነው። ዛሬም እንደ ትናንቱ 'እናንተ በረሃብ ስትሞቱ እኛ ጠግበን እንኑር' የሚለው ግለኛ አካሄድ ስላልለቀቃቸው ነው። ግና ይህ አስተሳሰብ ለዘመናት አብሯቸው የኖረ በመሆኑ በቀላሉ ሊለቃቸው ባይችልም ቅሉ፣ እነርሱ እንደሚያስቡት ሀገራችን ግን ህግን ያልተከተለ ግድብ በመገንባት ላይ አለመሆኗን ሊያውቁት ይገባል፣ ሃቁን ቢያውቁትም። ኢትዮጵያ ዓለም አቀፉ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ሁሉንም የተፋሰሱን ሀገራት ተጠቃሚ የሚያደርግ ይህዳሴ ግድብ በመገንባት ላይ የምትገኝ እንጂ እንደ እነርሱ በግለኝነት የምትመራ ሀገር አይደለችም።

ምንም እንኳን ቃል አቀባዩ ሚስተር ዋሲፍ ከአንድ ሀገር መንግስት በማይጠበቅ አሳፋሪ ሁኔታ ሀገራችን ግድቡን እንዳትገነባ የውጭ ዕርዳታ እንዳታገኝ እናደርጋለን ቢሉም፣

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በመገንባት ላይ የሚገኘው በህዝቡ ሁለንተናዊ ተሳትፎ ላይ መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግድቡ ቀደምት የተመጽዋችነት አስተሳሰብን የቀረፈ፣ ለፀረ - ድህነት ትግሉ ስኬት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው፣ የማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ስሜት የኮረኮረ፣ የይቻላል መርህን በተግባር ማዋል ያስቻለ ብሎም ከራስ አልፎ በሚደረገው ሽያጭ የህዝቡን ውለታ በዕድገት የሚመልስ በመሆኑ ታሪካዊነቱን የጎላ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል፡፡

እኛ ኢትዮጵያዊያን የምናድገው ለብቻችን አለመሆኑንም ሊገነዘቡት ይገባል። ኢትዮጵያውያን አብሮ መኖርን፣ ማደግንና መበልጸግን ከማንም በላይ የምንቀበልና የማንነታችን መገለጫም ነው። ልክ እንደ ግብፆች "ለብቻችን" ብለንም አናውቅም። እናም የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታችን ትኩረትም ማንንም ለመጉዳት ያለመ እንዳልሆነ ማንኛውም አካል ሊያውቅ ይገባል፡፡ አብሮ መብላትና ተያይዞ ማደግ የቆየ ኢትዮጵያዊ እሴት መለያ ባህሪ እንደሆነም ጭምር፡፡

ሀገራችን በተፈጥሯዊ የውሃ ሃብት አጠቃቀም ዓለም አቀፋዊው የእኩልነትና የፍትሃዊነት መርህን መሰረት ላደረገው የኢንቴቤው የስምምነት ማዕቀፍ ተግባራዊነት በግምባር ቀደምትነት የተሰለፈችውም ለዚሁ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ መላው ዜጎቿም ለህዳሴው ግድብ ግንባታ ስኬታማነት ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን እያበረከቱ የሚገኙት ደግሞ ግድቡ የጋራ ተጠቃሚነትን ሙሉ ለሙሉ የሚያረጋግጥ መሆኑን ጥንቅቀው ስለሚያውቁ ነው፡፡ ይሁንና ከበሬታችን ይህን ያህል ቢሆንም፤ በሀገራችን ሀብት ሰርቶ ለማደግና ለመለወጥ እንኳንስ የግብፅን ምክር እና ይሁንታ ቀርቶ የማንንም ፈቃድ አንጠይቅም፤ ልንጠይቅም አንችልም። ምክንያቱም ከጥንት ጀምሮ እንዲህ ዓይነቱ የቅኝ ግዛት አስተሳሰብን እንኳንስ ልንተገብረው ቀርቶ ልንሰማው ስለማንፈቅድ ነው።

ያም ሆነ ይህ ግን አሁንም ቢሆን ግብፆች የቅኝ ግዛት ውሎች ናፋቂነታቸው የትም እንደማያደርሳቸው ማወቅ ያለባቸው ይመስለኛል–የትም ቢሄዱ። ለምን ቢሉ የትናንቱ የሙባረክ መንግስት ከንቱ ጥረቶች ትምህርት ሊሆናቸው ይገባልና። ሙባረክ ኢትዮጵያ የህዳሴውን ግድብ እንዳትገነባ አንዴ በምግባረ-ሰናይ ድርጅትነት ስም ተሰልፈው በበሉበት የሚጮሁትን አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎችን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሀገራችንን ሆድ-አደር ባንዳ ተቃዋሚዎችን በመጠቀም ቢለፍፉና ቢያስለፍፉ ያመጡት አንዳችም ለውጥ የለም።

አዎ! እነርሱ ያሳቸው ቦታ ቢሄዱም ወሳኙ እውነት እንጂ ስብቀት ባለመሆኑ ቅቡል ሊሆኑ አይችሉም። ከሁሉም በላይ ደግሞ በቅኝ ግዛት ውሎች አማካኝነት "አብረን እንደግ" ባይና ሚዛናዊ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ እየገነባ ያለውን የህዳሴ ግድብ ከሰማይ በታች የሚያቆመው ኃይል አለመኖሩን በሰከነ አዕምሮ ማጤን ተገቢና ትክክለኛ ውሳኔ ይመስለኛል። እናም የካይሮ አስተዳደር ባለስልጣናት ያረጀ ያፈጀ የቅኝ ግዛት ውሎችን በማጣቀስ አላስፈላጊ ንትርክ ውስጥ ከመግባት ይልቅ ባቢያዊ ልማታዊ ትስስር መጠቀም ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ። "አንድም ጠብታ ውሃ አይነካብኝ፣...ምንትስ" ከማለት ይልቅ ከባቢያዊውን ልማታዊ ትስስር በጋራ የማደግ መርህን መከተል አዋጪ ነው። እርግጥም ለግብፆች የሚበጃቸው ወደ ትብብር ማዕቀፉ መምጣት እንጂ በቅኝ ግዛት ውሎች ተጀቡኖ ሁኔታውን ወደ ሌላ አቅጣጫ መምራት አይደለም። ቸር እንሰንብት።